# መቀሌ ዩኒቨርሰቲ የቻይና ቋንቋ በመጀመሪያ ዲግሪ ሰልጠና መስጠት ጀመረ

መቀሌ ህዳር 08/2005 የመቀሌ ዩኒቨርሰቲ የቻይና ቋንቋ በመጀመሪያ ዲግሪ ሰልጠና መስጠት መጀመሩን የዩኒቨርስቲው የህብረተሰብ ሳይንስና የቋንቋዎች ኮሌጅ ዲን አስታወቁ። የኮሌጁ ዲን ዶክተር ገብረእየሱሰ ተኽሉ ትናንት እንደገለጹት በዩኒቨርስቲው የቻይንኛ ቋንቋ ትምህርት መሰጠት መጀመሩ በኢትዮጵያና በቻይና መካከል ያለውን የዲፕሎማሲ፣ የባህልና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ከማጠናከሩም ባሻገር ዩኒቨርስቲው ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ ያሰችለዋል። የቻይና ቋንቋ ትምህርት በተያዘው ዓመት

በመጀመሪያ ዲግሪ ደረጃ 20 ተማሪዎችን ተቀብሎ እያስተማረ ሲሆን፣ በምስክር ወረቀት ደረጃም ቋንቋውን ለመማር ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች በማስተማር ላይ ይገኛል። ሚስተር ዣንግ ሻለይ የቻይና ቋንቋ ትምህርት አሰተባባሪ በበኩላቸው ትምህርቱ በኢትዮጵያ በመቀሌና አዲስ አባባ ዩኒቨርስቲዎች በመጀመሪያ ዲግሪ እየተሰጠ እንደሚገኝ ጠቅሰው ቋንቋው ሁለቱ ሀገራት ለሚያደርጉት የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የንግድ ልውውጥ እና የስራ እድሎች ለመፍጠር የጎላ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

በተለይ የቋንቋ እውቀት ያላቸው ተማሪዎች የቻይና መንግሰትና ባለሀብቶች በሚካሄድዋቸው የልማት ስራዎች በአስተርጓሚነትና በባለሙያነት ተቀጥረው እንዲያገለግሉ ከፍተኛ ድርሻ አለው ብለዋል። የቻይና ቋንቋ ኢትዮጵያን ጨምሮ በበርካታ የአፍሪካ ሀገራት በዩኒቨርስቲ ደረጃ እየተሰጠ እንደሚገኝ ገልፀው በቀጣይ የሁለተኛ ዲግሪ በስኮላር ሽፕ የትምህርት ፕሮግራም እድል እንደሚመቻች ገልጸዋል። የመቀሌ ዩኒቨርስቲ በቻይናና በጃፓንኛ ቋንቋዎች ከ700 በላይ ተማሪዎች በሴርቲፊኬት ያስመረቀ ሲሆን በጃፓንኛ ቋንቋም የመጀመሪያ ዲግሪ ትምህርት እንደሚጀመር ዶክተር ገብረ እየሱስ አስታውቀዋል።